# ትንቢተ ዕንባቆም (41)

## ጥናት አንድ ዕንባቆም 1፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላክ ጥያቄ ይዘን ወደ እርሱ መምጣታችን የሚያስቆጣውና የሚያሳዝነው ሳይሆን፤ አዕምሯችንን ለሚያስጨንቁት ጥያቄዎቻችን በመንፈስ ቅዱሱ አማካኝነት መልስ ለመስጠት ሁልጊዜ ዝግጁ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በመጠባበቂያ ላይ እቆማለሁ፣ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ አቆያለሁ፣ ምን እንደሚለኝ፣ ለክርክሩም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ፡፡›› ዕን 2፡1

1. ዕንባቆም 1፡1-17 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ላይ እንባቆም እግዚአብሄርን የሚጠይቀው ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው? ‹‹እስከ መቼ›› እያለ እንባቆም ከሚናገረው አነጋገር በስተኂላ መረዳት የምንችለው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ፤ እግዚአብሄር አምላክ ጸሎትህን ከመስማት የዘገየና ግድ እንደሌለው ሆኖ የተሰማህ ጊዜ ይኖር ይሆን?
2. እንባቆም በህዝቡና በአካባቢው የሚያየው ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ምንድነው? በአካባቢው ስለሚያየው ፍትህ መጓደል፣ ግጭት፣ ግፍና የመሳሰሉት ክፉ ምግባራት እንባቆም የወሰደው እርምጃ ነበረ ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
3. እንባቆም በዙሪያው የሚመለከተውን ክፋትና ርኩሰት እንዲቆም የወሰደው እርምጃ በእንባቆም አመለካከት ፍሬ አፍርቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? የእንባቆምን ጥያቄዎች ስንመለከት፤ ይህ ሰው በህይወቱ ዋጋ የሚሰጠውና የሚያንገበግበው አንድ ነገር አለ ብትባል ምንድነው ትላለህ?
4. እግዚአብሄር ለእንባቆም ጥያቄ ምላሽ አድርጎ የሰጠው በቁ5-11 ላይ የሰጠው የትኛውን ጥያቄውን እንደመለሰለት ነው የምታምነው? ይህ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናነበው የእግዚአብሄር ምላሽ ለእንባቆም በቂ የሆነ መልስ ሆኖለታል ብለህ ትገምታለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
5. በቁ5-11 ላይ በክፋትና በጭካኔ፣ በፍትህ ማጓደል የተበከለውን የእንባቆምን ህዝብ ለመቅጣት እግዚአብሄር ሊጠቀምበት ስላለው ህዝብ የሞራል ባህርይ ምን እናነባለን? የቅጣት በትር አድርጎ የሚጠቀምባቸውን ህዝቦች ባህርይ ስትመለከት ለእንባቆም ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ የማይችሉበት ምን ምክንያት ታያለህ?
6. ቁ12-13 ላይ ነብዩ እንባቆም ስለ እግዚአብሄር ማንነት የሚናገራቸውን የተለያዩ ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር፡፡ በተለይ በቁ13 ላይ የእንባቆም ሌሎቹ ጥያቄዎቹ ምን የሚሉ ናቸው?
7. ቁ14-17ትን ስታነብ እንባቆም ስለ እግዚአብሄር አሰራር የተሰማው ስሜት ምን ይመስላል? እንባቆም ከእግዚአብሄር ያገኘው መልስ የጠበቀው ዓይነት መልስ ይመስልሃል ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ለወገኖች አስረዳ፡፡
8. በዚህ በምዕራፍ አንድ ላይ በተመለከትነው ነብዩ እንባቆም በልቡ የሞላውን ጥያቄውን ወደ እግዚአብሄር ማቅረቡ ሲነቅፈው ወይም ሲቆጣው ታያለህ ወይ? አንተስ ጥያቄህን ወደ አምላክህ ማቅረብ ያስፈራሃል ወይ? ጌታችን ጥያቄ ይዞ ወደርሱ ለሚመጡት ልጆቹ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መልስ መስጠት እንጂ ለምን ጠየከኝ በሚል የሚቆጣ አምላክ ስላልሆነ አክብሮት በሞላበት ድፍረት ጥያቄህን ለማቅረብ ዙፋኑ ሁሌም ክፍት ነው፡፡

# ጥናት ሁለት ዕንባቆም 2፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- በራሳችንም ህይወት ሆነ በአካባቢያችን እየሆኑ ያሉት ብዙ ነገሮች ባይገቡንና ጥያቄ በሚፈጥሩብን ጊዜ ሁሉ፤ እግዚአብሄር በመቅደሱ ከፍ ብሎ እንዳለና ፍጥረት ከቁጥጥሩ ውጭ እንዳልወጣ ራሳችንን ለማሳሰብ፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድር ሁሉ በፊቱ ጸጥ ትበል፡፡›› ዕን 2፡20

1. ዕንባቆም 2፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ ነብዩ እንባቆም በቁ1-3 በተለይም በመጀመሪያው ቁጥር ላይ ሊያደርግ የወሰነው ነገር ምን ነበረ? በኢሳ 39፡5-7 ላይ ኢሳይያስ በተናገረውና በዚህ መጽሃፍ ውስጥ በተለይም በ2፡1-3 በምናነበው መሃል ለአንተ የሚታይህ ምን ልዩነት አለ?
2. እግዚአብሄር ለዕንባቆም የሰጠውን መገለጥ ሰዎች ሁሉ እንዲያዩትና እንዲያነቡት መፈለጉን የገለጸበት መንገድ ምንድነው ትላለህ? በቁ2-4 ስናነብ ዕንባቆም እንዲያስተላልፍ የተሠጠው የእግዚአብሄር መልዕክት ለሰዎች የማያሻማና ለመረዳት የማያስቸግር እንዳልነበረ የሚያረጋግጥልን ቃል የትኛው ነው? እግዚአብሄር ቃሉን እንድንረዳ እንጂ በቃሉ ግራ እንድንጋባ እንደማይፈልግ ልናውቅ ይገባናል፡፡
3. ቁ3 ላይ ‹‹ራዕዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፣ ስለ መጨረሻውም ይናገራል›› የሚለው አነጋገር ለምንድነው ለዕንባቆም እምነት ማጠናከሪያ ሊሆን የሚችለው? በቁ4 ላይ ‹‹ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል›› የሚለውን አነጋገር እንባቆም የተጠቀመው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ6-11ድን ስናነብ በቁ6 ላይ የምናየው ወዮታ የተነገረው ለምን ዓይነት ሰዎች ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ሌላው የምናነበው ወዮታ በየትኛው ቁጥር ላይ እናገኘዋለን? ይህስ ሁለተኛው ወዮታ በምን ዓይነት ሰዎች ላይ ያተኮረ ነው? አንተስ ከጠላትህ ለማምለጥ የምትሞክረው አምላክህን መታመኛ በማድረግ ወይስ ከፍ ብለው በሚታዩ የተለያዩ ነገሮች በመደገፍ?
5. በቁ12-14 ውስጥ የምናየው ወዮታስ በነማን ላይ ያተኮረ ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር የወሰነውና እንደሚከናወን ትንቢት አድርጎ ነብዩ እንባቆም የሚናገረው አንድ እውነት ምንድነው? በሌላ ገጽታው የሚፈጸም በዚሁ ክፍል ሌላ ነብዩ የሚነግረን ትንቢት ምንድነው?
6. በቁ6 ላይ ‹‹…አሁን ደግሞ ተራው የአንተ ነውና ጠጣ፤ ሃፍረተ ሥጋህም ይገለጥ›› በማለት የሚነገረው ትንቢት በገላትያ 6፡7 ላይ ሰፍሮ የምናየውን አምላካዊ እውነታ የሚያንጸባርቀው በምን መንገድ ነው? ሰው የዘራውን ሲያጭድ ያየህበት ሁኔታ፤ ወይም ደግሞ ይህ እውነት በአንተ ላይ ተከናውኖ ከሆነ ለወገኖች አካፍል፡፡
7. የመጨረሻውና በቁ18 ላይ የተነገረው ዋይታ ለምን ዓይነት ሰዎች ነው? በቁ19 ላይ ነብዩ እነዚህን ሰዎች የሚጠይቀው አንድ ጥያቄ ምን የሚል ነው? ይህንን ሲጠይቅ ምን ሊል ነው የፈለገው ብለህ ታስባለህ? ነብዩ ለራሱ የሰጠው መልስ ምን የሚል ነው?
8. በቁ20 ላይ ‹‹እግዚአብሄር ግን…›› በማለት መናገር የጀመረው አምላኩን ከምን ጋራ እያነጻጸረ ነው? በቁ20 ላይ ነብዩ እንባቆም ራሱንም ጨምሮ ምድር ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት ጸጥ እንዲል ሲያዝ፤ ለእርሱ ለራሱ ከዚህ አነጋገሩ እያስተላለፈ ያለው መልዕክት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በዙሪያችንና በራሳችንም ህይወት ጭምር እየሆነ ያለው ነገር ባይገባንም እንኳን፤ እግዚአብሄር በመቅደሱ ሆኖ ፍጥረትን እንደሚገዛ አስታውስ፡፡

# ጥናት ሶስት ዕንባቆም 3፡1-19

የጥናት ዓላማ፡ በእጃችን ያለውን ንብረትና በባንክ ያለን ገንዘብ የደስታችን ምንጭ አድርገን የምናይ ከሆነ ምስኪኖች ነን፤ ነገር ግን በነህምያ 8፡10 እንደምናነበው የእግዚአብሄር ደስታ ሃይላችን ስለሆነ፤ እርሱን የደስታችን ምንጭ ልናደርገውና በእርሱ ሃሴት ማድረግን መለማመድ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እኔ ግን በእግዚአብሄር ደስ ይለኛል፤ በድነቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ፡፡›› ዕን 3፡18

1. ዕንባቆም 3፡1-19 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ2 ላይ እንባቆም ስለ እግዚአብሄር የሚናገረው ምን በማለት ነው? ከዚህ ጋራ በማስታከክ በዚሁ ቁጥር ላይ ነብዩ እግዚአብሄርን የሚጠይቃቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እግዚአብሄር በቁጣ ጊዜ እንኳን ምህረትን ማሰብ የሚችል አምላክ መሆኑን አንተስ ተገንዝበኸዋል ወይ?
2. በቁ3-15 ላይ እግዚአብሄር ጠላቶቹን እንዴት እንደሚበቀል በዝርዝር ይናገራል፡፡ በተለይም ቁ13ትን ስንመለከት ይህ የእንባቆም አነጋገር ዘሬ በእኛ ጠላት በዲያቢሎስ ላይ ካደረገው ጋራ በምን ዓይነት ልናነጻጽረው እንደምንችል ተናገር፡፡
3. መጥቶባቸው የነበረውን የጠላት ዓይነት እንባቆም በቁ14-15 ላይ ምን በማለት ነው የሚገልጸው? እግዚአብሄርስ ይህንን ከባድ፣ ሃይለኛ እጅግ ክፉ ጠላታቸውን አጥፍቶ ከመንገድ ለማስወገድ የተጠቀመበት መንገድ ምን እንደሆነ ነው ነብዩ የሚነግረን? ሕይወትህን መለስ ብለህ ስታየው፤ አስጨናቂውን ጠላትህን እግዚአብሄር ተገልጦ በራሱ መሳሪያ ማለትም አንተን ለማጥፊያ ያመጣውን ነገር ለደህንነትህ ሲጠቀምበት አይተህ የምታውቅ ከሆነ ለወገኖች አካፍል፡፡
4. በቁ16 ላይ ‹‹እኔ ሰማሁ›› በማለት ነብዩ የሚናገረው፤ የሰማው ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ? ይህ እንባቆም ሰማሁ የሚለው ነገር በነብዩ ስሜት ላይ ያስከተለው ነገር ምን ነበረ?
5. በቁ17 ላይ በሰው ልጆች ላይ ሊደርሱ የሚችሉና እንባቆም የደረደራቸው ችግሮች ምን ምንድናቸው? በዚህ ዝርዝር ውስጥ የምናነባቸው አብዛኛዎቹ ከእኛ ህይወት ጋራ ስናያቸው ብዙም ትርጉም ላይሰጡን ይችላሉ፡፡ በእኛ ህይወት ውስጥ የነዚህኑ ያህል ኑሮአችንን ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ የምትሏቸውን ነገሮች በማንሳት ውይይት አድርጉባቸው፡፡
6. በቁ17 ላይ ነብዩ እንባቆም የሚዘረዝራቸው ሁኔታዎች በኢዩኤል 1፡12 ላይ ስንመለከት በሰው ስሜት ላይ ሊያስከትሉት ስለሚችሉት ነገር ምን ታያለህ? ሰዎችን ወደዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሊጨምሩ የሚችሉት እነዚህን ነገሮች የእርሱንም ልብ ወደዚህ ደስታን ወደማጣት ስሜት ውስጥ እንዳይከቱት የተጠቀመበት በቁ18 ላይ የምንመለከተው መንገድ ምንድነው?
7. በቁ18 ላይ ‹‹እኔ ግን›› ብሎ ሲናገር በተለይም ከኢዩኤል 1፡12 በማነጻጸር ስናነበው ራሱን ከማን ጋራ በማስተያየት የሚናገር ይመስልሃል? ነብዩ እግዚአብሄርን በቁ19 ላይ የሚያይበትና ለህይወቱ ሆኖ የሚያገኘው ነገር ምን ይመስላል?
8. ቁ19ን ስናነብ እግዚአብሄር ሃይሉ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ቁ18 ላይ ለእንባቆም ደስታውና ሐሴቱ አድርጎ የሚነግረን ማንን ነው? የደስታህ ምንጭ እግዚአብሄር ነው ወይስ በእጅህና በባንክ ያለህ ንብረት? ያለህ ነገር ሁሉ ከእጅህ ቢጠፋ እንኳን ማንም ሊወስድብህ የማይችለውን በክርስቶስ የሚገኘውን ደስታ አጥብቀህ ልትይዝ ያስፈልግሃል፡፡